የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 14
ADDIS ABABA 7th January 2009

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፩
የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ....................................... ገፅ ፬ሺ፬፻፳፫

ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፩

## የኢንዱስትሪ ብክለትን ለመከላከል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፳ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፤

፩. "ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት" ማለት የሥራ ፈቃድ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል የመንግሥት አካል ነው ፤

፪. "ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት" ማለት እንደ ሁኔታው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ነው ፤

፫. "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/ ፲፱፻፺፬ መሠረት የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.80

CONTENTS

Regulation No. 159/2008
Prevention of Industrial Pollution council of Ministers Regulation.................................. Page 4423

REGULATION No. 159/ 2008

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE PREVENTION OF INDUSTRIAL POLLUTION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation NO. 471/2005 and Article 20 of the Environmental Pollution Control Proclamation No. 300/2002.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Prevention of Industrial Pollution Council of Ministers Regulation No. 159/2008"

2. *Definitions*

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1. "competent licensing agency" means any federal or regional government organ empowered by law to issue business license;
2. "competent environmental organ" means any federal or regional environmental protection agency;
3. "Authority" means the Environmental Protection Authority established pursuant to Proclamation No. 295/2002;

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመ ለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል ፤

፭. "ነባር ፋብሪካ " ማለት ይህ ደንብ ከፀናበት ቀን በፊት ወይም በፀናበት ቀን እየሰራ የነበረ ፋብሪካ ወይም ፋብሪካ ለመስራት የሥራ ፈቃድ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ፕሮጀክት ነው፡

፮. "ብክለት" ማለት በዚህ ደንብ ፣ አግባብነት ባለው የአካባቢ ደረጃ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገ ማንኛውንም ግዴታ ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውንም አካባቢ ክፍል ቁሳዊ ፣ ጨረራዊ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረ ነገራዊ፣ ሥነ-ሕይወታዊ ወይም ሌላ ባሕሪይን በመለወጥ የተፈጠረ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤

፯. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ተቋም ነው ፤

፰. በወንድ ጾታ የተነገረው ማንኛውም አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል ።

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በተዘረዘረ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ የሚካተት ፋብሪካን ወይም ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ያሳወቀው ፋብሪካን በሚመለ ከት ፋብሪካው እስሚዘጋበት ወይም ከተዘጋ በኋላም ቢሆን ሥልጣን ያለው የአካባቢ መሥሪያ ቤት እስከወሰነው ተጨማሪ ጊዜ ማብቂያ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

፬. <u>አጠቃላይ ግዴታ</u>

፩. የዚህ ደንብ ድንጋጌ የሚመለከተው ፋብሪካ በካይ ነገር እንዳይመነጭ የማድረግ ፣ የማይ ቻል ከሆነም በሚመለከተው የአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ ሳያልፍ አመንጭቶ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የማስወገድ ግዴታ አለበት ።

፪. ማንኛውም ፋብሪካ መሣሪያው፣ ግብአቱና ምርቱ በአካባቢና በሰውና በእንስሳት ጤንነት ላይ ጉዳት እንዳይከተል የማድረግ ግዴታ አለበት ።

፫. ማንኛውም ፋብሪካ በይዞታው ያለን ማንኛውም አደገኛ በካይ ቆሻሻ፣ ግብዓት ወይም ምርት ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት ።

፬. ማንኛውም ፋብሪካ አደገኛ በካይ ቆሻሻ፣ ግብዓት ወይም ምርት ቢጠፋበት ወዲያውኑ ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት ።

4. "region" means any region referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, for the purpose of this Regulation, includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

5. "existing factory" means a factory that is under operation or a project to which an application to obtain a license to establish a factory has been submitted before or on the date of entry into force of this Regulation;

6. "pollution" means any condition which is hazardous or potentially hazardous to human health, safety or welfare or to living things created by altering any physical, radioactive, thermal chemical, biological or other property of any part of the environment in contravention of any condition, limitation or restriction made under this Regulation, the relevant environmental standard or under any other relevant law;

7. "person" means a natural or juridical person:

8. Under this Regulation any expression in the masculine gender shall also include the feminine gender..

3. *Scope of Application*

The provisions of this Regulation shall apply to a factory which is in an industrial sector listed in a directive issued under this Regulation or has been notified by the competent environmental organ in accordance with sub-article (5) of Article 4 of this Regulation, until it ceases to operate or until such additional time as has been determined by the competent environmental organ.

4. *General Obligations*

1. A factory subject to this Regulation shall prevent or, if that is not possible, shall minimize the generation of every pollutant to an amount not exceeding the limit set by the relevant environmental standard and dispose of it in an environmentally sound manner.
2. Even factory shall have the obligation to handle equipment, inputs and products in a manner that prevents damage to the environment and to human and animal health.
3. Every factory shall notify the competent environmental organ any potentially pollutant, input or product under its possession.
4. If any factory loses a potentially pollutant, input or product it shall immediately notify the competent environmental organ.

፭. በዚህ ደንብ የማይሸፈን የፋብሪካ ዓይነትም ቢሆን ከፋብሪካው እንቅስቃሴ ሊከተል የሚችል ጠንቅን የሚያስቀር እርምጃ እንዲወስድ ሥልጣን ያለው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ሊወስን ይችላል ፡፡

፮. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በአካባቢ ደረጃ የተደነገገውን የብክለት ጣራ በማለፍ ከፍተኛ አደጋ ማስከተሉ እንደማይቀር ላመነበት ፋብሪካ የአስጊ ሁኔታውን መከሰት የሚያስቀር እርምጃ እንዲወስድ የጽሑፍ ትዕዛዝ መስጠት አለበት ፡፡

፭. የሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ለፋብሪካ የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ልቀቱ በካይ አለመሆኑን ፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ መሆን አለበት ፡፡

፮. የፈቃድ ግዴታን ስለመለወጥ

፩. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ተሰጥቶ በነበረ ፈቃድ የተመለከቱ ግዴታዎችን ለመለወጥ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ፤

ሀ) ፋብሪካው የአመራረት ዘዴውን ሲለውጥ ወይም መስፋፋት ሲያደርግ ፤

ለ) ፋብሪካው ሥራውን በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ሳይጀምር ሲቀር ወይም

ሐ) ከባድ እንድምታ ያለው ቀደም ሲል ያልተ ጤነ እውነታ ሲከሰት ነው ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጥ ትዕዛዝ ትዕዛዙ የተሰጠበትን ምክንያ ትና ተፈፃሚ የሚሆንበትን የጊዜ ገደብ ማመ ልከት አለበት ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ ተገቢነት የሚቃወም የፋብሪካ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ወኪል ትዕዛዙ ከደረሰው ዕለት አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በጽሑፍ ለማቅረብ ይችላል ፡፡

፬. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በቀረበለት ተቃውሞ ላይ በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት ፡፡

፯. ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ

፩. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ ደንብ መሠረት እንዲሟላ የተዘረዘረ የፈቃድ ግዴታ አለመከበሩን ሲያውቅ የፋብሪ ካው የሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰ ረዝ መወሰን አለበት ፡፡

5. Even if a factory is not subject to the provisions of this Regulation, the competent environmental organ may require it to take appropriate measures in order to eliminate any risk that might emanate from its operation.

6. The competent environmental organ shall issue a written order to a factory that it believes will entail substantial damage by transgressing the limit set by the environmental standard to take measures to remove the risk.

5. *Licensing*

The competent licensing agency can grant a license to a factory after verifying that the effluent is not a pollutant or will not exceed the limit set under the relevant environmental standard and it will not entail damage if released into the environment.

6. *Varying Licensing Requirements*

1. The competent environmental organ may order a variation of the conditions of a license that has been granted whenever:

   a) the factory introduces change in its operational technique or undertakes an expansion;

   b) the factory does not commence its operations within the set time limit; or

   c) an unforeseen fact of serious implication is realized.

2. Any order issued pursuant to sub-article (1) of this Article shall state the reason for the issuance of the order and the time limit within which it shall be implemented.

3. The owner or legal representative of any factory who challenges the appropriateness of the order issued pursuant to sub-article (2) of this Article may, within 30 days from receipt of the order, submit a written complaint to the competent environmental organ.

4. The competent environmental organ shall. Within 30 days, issue its decision on the complaint submitted to it in accordance with sub-article (3) of this Article.

7. *Suspension or Cancellation of License*

1. The competent environmental organ shall suspend or cancel the license of a factory whenever it finds out that the conditions of the license set in accordance with this Regulation have not been complied with.

፪. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተላለፈ ቢሆንም የፋብሪካው የሥራ እንቅስቃሴ መቀጠል ከፍተኛ ብክለት እንደሚያስከትል ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ሲያምን የሥራ ፈቃዱ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ መወሰን አለበት ::

፫. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የወሰነበትን ምክንያትና ከመቼ አንስቶ ተፈፃሚ እንደሚሆን ሥልጣን ለተሰጠው የፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት :: ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤቱም ውሳኔውን ማስተግበር አለበት ::

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተላለፈው ውሳኔ ተገቢ አለመሆኑን የሚቃወም ፋብሪካ ውሳኔው ከደረሰው ዕለት አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል ::

፭. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የቀረበለትን የቅሬታ ማመልከቻ ከተቀበለበት ዕለት አንስቶ በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ አሳልፎት የነበረውን ውሳኔ እንዲሻሻል ፣ እንዲሰረዝ ወይም እንዲፀና ማድረግ አለበት ::

## ፰. አደጋ የመከላከያ ሥርዓት

፩. ይህ ደንብ የሚመለከተው ማንኛውም ፋብሪካ የአደጋ መከላከያ ዘዴ አዘጋጅቶ መተግበር አለበት ::

፪. ፋብሪካው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተዘጋጀውን የአደጋ መከላከያ ዘዴ ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤቱ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት ::

## ፱. የአካባቢ ደህንነት ክትትል

፩. ይህ ደንብ የሚመለከተው ፋብሪካ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጥበትን የራሱን የውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ አዘጋጅቶ መተግበር አለበት ::

፪. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት አስፈላጊነቱን ካመነበት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ መሠረት በወጣው መመሪያ ባልተጠቀሰ ዘርፍ በተሰማራ ፋብሪካም ላይ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ ይችላል::

## ፲. የሕዝብ ቅሬታ

፩. ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማንኛውም ሰው ጉዳዩ እንደሚመለከተው ማስረዳት ሳይጠበቅበት ብክለትን አስመልክቶ የሚያቀርበቀው ቅሬታ የሚስተናገድበትን ዘዴ ያዘጋጃል::

2. The competent environmental organ shall, despite the factory's observance of the requirements set under the provisions of this Regulation, suspend or cancel a license if it has reason to believe that the continuation in operation of the factory may entail serious pollution.

3. The competent environmental organ shall. when it decides to suspend cancel a license in accordance with sub-article (1) or (2) of this Article, notify the competent licensing agency its reason and the time when it shall be implemented. The licensing agency shall ensure the enforcement of the decision accordingly.

4. The owner or legal representative of any factory who challenges the appropriateness of the decision issued pursuant to sub-article (3) of this Article may, within 30 days from receipt of the decision, submit a written complaint to the competent environmental organ.

5. Within 30 working days from the date of receipt of any challenge submitted to it in accordance with sub-article (4) of this Article, the competent environmental organ shall amend, cancel or uphold its decision.

## 8. *Emergency Reponses system*

1. Any factory subject to the provisions of this Regulation shall prepare and implement an emergency response system.

2. The emergency response system prepared pursuant to sub-article (1) of this Article shall be notified to the competent environmental organ by the factory.

## 9. *Monitoring of Environmental Safety*

1. A factory subject to the provisions of these Regulation shall, with a view to ensuring its compliance with this Regulation, prepare and implement its own internal environmental monitoring system.

2. The competent environmental organ may, if it deems it necessary, apply the provisions of sub-article (1) of this Article even if the industrial sector of the factory is not listed in a directive issued pursuant to Article 3 of this Regulation.

## 10. *Public complaints*

1. The competent environmental organ shall prepare a mechanism to respond to any person who complains concerning pollution without requiring him to prove vested interest.

፪. ብክለትን አስመልክቶ ቅሬታ የቀረበለት ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ጉዳዩን በማጣራት የወሰደውን እርምጃ በ፺ ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት ::

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተወሰደ እርምጃ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በጽሑፍ ለማቅረብ ይችላል፡፡ የበላይ ኃላፊውም ቅሬታው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ በቀረበው ቅሬታ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት ::

፲፩. <u>የብክለት አያያዝ መረጃ</u>

፩. ይህ ደንብ የሚመለከተው ማንኛውም ፋብሪካ የሚገለገልበትን መሣሪያና የተጠቀመበትን ግብዓት፣ ያመረተውን ምርት፣ ያመነጨውን በካይ ነገር ፣ በካይ ነገሩን ያስወገደበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግቦ መያዝ አለበት ::

፪. ማንኛውም ፋብሪካ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችን እንዴት እየተገበረ እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ ሥልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ ማቅረብ አለበት ::

፫. ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት ዓመቱ ማውጣት አለበት ::

፲፪. <u>ስለ ነባር ፋብሪካዎች</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት በወጣ መመሪያ በተዘረዘረ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በ፭ ዓመታት ውስጥ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ ማክበር አለበት ::

፪. በዚህ ደንብ መሠረት በወጣ መመሪያ በተዘረዘረ የኢንዱትር ዘርፍ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ነባር ፋብሪካ የዚያን ደንብ ድንጋጌዎች የሚያሟላበትን ሁኔታ ለመወሰን የአካባቢ ኦዲት ማካሄድና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅቶ መተግበር አለበት ::

፫. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ ሊወገድ የማይቻል ሆኖ ከተገኘ ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይህንኑ አሉታዊ ትፅዕኖ ለማስወገድ ያስችላል ብሎ ያመነበትን እርምጃ መውሰድ አለበት ። ይህም እርምጃ ፋብሪካውን ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር ወይም ደግሞ እንዲዘጋ መወሰንን ሊጨምር ይችላል፡፡

2. The competent environmental organ to which a complaint on pollution has been submitted shall investigate the case and take measures and notify to the complainant within 90 days.

3. Any person dissatisfied by the measure taken in accordance with sub-article (2) of this Article may submit a complain notice to the head of the competent environmental organ in writing within 30 days of the issuance of the decision. The head of the competent environmental organ shall issue his decision within 30 days following the receipt of the complain notice.

11. *Information on Pollution Management*

1. Any factory subject to this Regulation shall keep written information describing the equipment and input it has used, the product it has produced, the pollutant it has generated, and the disposal mechanisms it has used to dispose of the pollutant and other related matters.

2. Every factory shall submit to the competent environmental organ an annual report describing how it is complying with the provisions of this Regulation.

3. The Authority shall issue a report on the amount, source, movement and disposal of pollutants in Ethiopia at least every five years.

12. *Existing Factories*

1. An existing factory that is in an industrial sector listed in a directive issued pursuant to this Regulation shall, within a maximum of 5 years, fully comply with the provisions of this Regulation.

2. Every existing factory that is in industrial sector subject to this Regulation shall, with a view to complying with this Regulation, undertake environmental audit, and prepare and implement an environmental management plan.

3. The competent environmental organ shall. if it is not possible to avoid the adverse impacts likely to emanate from the operation of the factory within the time limit specified in sub-article (1) of this Article take any measure it deems appropriate to avoid the adverse impacts. The decision may include either the relocation or closure of the factory.

፲፫. የኃላፊነት ድርሻ

፩. የሥራ ፈቃድ የመስጠቱ ድርሻ የፌዴራል መንግሥት አካል የሆነን ፋብሪካ በተመለከተ ይህንን ደንብ የማስፈፀም ኃላፊነት የባለሥል ጣኑ ይሆናል ፡፡

፪. የሥራ ፈቃድ የመስጠቱ ድርሻ የክልል መን ግሥት አካል የሆነን ፋብሪካ በተመለከተ ይህንን ደንብ የማስፈፀም ኃላፊነት የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሆናል ፡፡

፲፬. ቅጣት

በወንጀል ሕግ የአካባቢ ብክለትን በሚመለከት የተደነገጉት የቅጣት ድንጋጌዎች ይህንን ደንብ ለማስተግበር ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ፡፡

፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

13. *Responsibility*

1. It shall be the responsibility of the Authority to enforce this Regulation with respect to a factory licensed by the Federal Government.

2. It shall be the responsibility of the regional competent environmental organ to enforce this Regulation with respect to a factory licensed by a regional government.

14. *Penalties*

The provisions of the Criminal Code on environmental pollution shall apply for the enforcement of this Regulation.

15. *Effective Date*

This Regulation shall come into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 7th Day of January, 2009.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA